

የቅዱስ አትናቴዎስ ሀይወቱ እና አስተምህሮቱ

‹‹ሰላም ለአትናቴዎስ ከመ ላዕሌሁ ተነበዩ፡፡ ደቂቀ ክርስቲያን ኩሎሙ እንዘ ይትዋነዩ፡፡ ሊቀ ጳጳሳት ዘኮነ ወምእመነ ክርስቶስ ዲበ ንዋዩ፡፡ ወበእንተ ዘበጽሑ ስደት እመንበረ ክብሩ ወእበዩ፡፡ ሐዋርያዌ በኵሉ ዓያዩ፡፡›› አርኬ (በስንክሳሩ መጨረሻ ሊቁ አርከ ሥሉስ እንደደረሰው)

የቅዱስ አትናቴዎስ ህይወቱ እና አስተምህሮቱ ዳሰሳ

አዘጋጅ፡- በአሰላ ደ/መ/መ/ቤ/ክ የሁለተኛ እና የመሰናዶ ተማሪዎች ጉባዔ

1. አዲስዓለም ፋንታሁን
2. ሩሀማ ደምሴ
3. አማኑዔል ፀጋዬ
4. ውዳሴ ማርያም ክፍሌ
5. ቅድስት አስቻለው

ነሐሴ

2008

ማውጫ

ሀ. መቅድም

ለ. መግቢያ

ሐ. ምስጋና

1. ምዕራፍ አንድ
   የቅዱስ አትናቴዎስ ውልደት እና እድገቱ
2. ምዕራፍ ሁለት
   ጉባኤ ኒቂያ
   2.1 እስክንድርያ
   2.2 ቅድመ ኒቂያ
   2.3 በጉባዔ ኒቂያ ላይ....
   2.4 አርዮስ ያነሳቸው ሀሳቦች በኒቂያ ጉባኤ
3. ምዕራፍ ሦስት
   የቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ፓትርያርክ መሆን
   3.1 ስደቱ
4. ምዕራፍ አራት
   ስለ አትናቴዎስ
5. መደምደሚያ
   የገጠሙን ችግሮች

መ. ዋቢ መጽሐፍት

ሀ. መቅድም

ከሁሉ አስቀድመን በምህረትና በቸርነቱ ጠብቆ ይሔንን አጭር ዳሰሳ እንድናዘጋጅ ለፈቀደ ለአምላካችን ክብርና ምስጋና ይግበው። በምልጃዋ የማታሰፍረን እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ስሟ በኛ በደካሞቹ ዘንድ የተመሰገነ ይሁን!

በክርስቶስ ክርስቲያን የተባልን በ40 እና በ80 ከአብራከመንፈስ ቅዱስ ተወልደን ልጆቹ ያደረገን ቤተ መቅደሱ አኛ ነን። በተለይ በዚህ ዘመን ወጣቱን ማዕከል ያደረገ በእምነቱ ደካማ እንዲሆን የሚያደርጉ ብዙ ፍላፃዎች ከየአቅጣጫው እየተወረወሩ ይገኛሉ። እነዚህን ጥቃቶች መከላከል የሚቻለው ወጣቱን በቤተ-ክርስቲያን በመሰብሰብ እና የቃሉን ጋሻ እና ጦር በማስታጠቅ ነው።

ወጣቱን በመሰብሰብ በኩል ከሰንበት ትምህርት ቤቶች ቀጥሎ በተለይ በከተማችን አሰላ ከፍተኛ ስራ በመስራት ላይ ያለው የ2^{ተኛ} ደረጃና የመሰናዶ ተማሪዎች ጉባዔ ነው። ይህ ጉባዔ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ወጣቱ በተለይ ተማሪው በእንግዳ ደራሽ በወፍ ዘራሽ ትምህርት እና አስተሳሰብ እንዳይወሰድ በትዕግስት እና በማስተዋል ዘመኑን እንዲዋጅና እንዲራመድ አምላክ በፈቀደ መጠን እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።

የቀደመ አባቶችን ተጋድሎ እና ክርስትናዊ ህይወት እንዲሁም ትምህርቶቻቸውን ማወቅ ለህይወታችን እና ለክርስትናችን እጅግ በጣም ጠቃሚ ነው። መጽሐፍ እንዲ እንዲል ‹‹ የቀደመችውንም መንገድ ጠይቁ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደሆነች እወቁ በእርሷም ላይ ሂዱ ለነፍሳችሁም እረፍት ታገኛላችሁ ›› ት.ኤር 6፡16 ስለዚህ በቀደመ አባቶቻችን መንገድ ላይ ለመቆም የእነሱን መንገድ ማወቅ ያስፈልጋል።

እኛም በዚህች አጭር ዳሰሳ ስለ ቅዱስ ሐዋርያ አትናቴዎስ ህይወቱ እና አስተምህሮቱ አንብበን አባቶችን ጠይቀን ወንድሞችን አማክረን አቅርበናል። ይህ ዳሰሳ ክብዙ በጠቂቱ በሚባል መልኩ እኛን ለቀጣይ ስራ ያነሳሳናል በሚል እንጂ ሙሉ ታሪኩንም ሆነ፤ ትምህርቱን እንዳላካተተ እናምናለን። በመሆኑም እንደ ዳረጎት (ጭማሪ) ታስባ የቀረበች ናት። ከብረት ዝገት ከሰው ስህተት አይጠፋምና የተሳሳትነውን እያረማቸሁ ያጎደልነውን እየሞላችሁ በመንፈስ ሆናችሁ እንድታነቡት በልዑል እግዚአብሔር ስም እንጠይቃለን

ለ. መግቢያ

ይህ ዳሰሳ በአምስት ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲሆን በውስጡም የቅዱስ አትናቴዎስ ከልደቱ ጀምሮ አመጠራሩ፣ እድገቱ፣ ሲመተ ድቁና ፣ጉባዔ ኒቂያ፣ በጉባዔው ስለተነሱ ሐሳቦች ፣ስደቱን እንዲሁም ለቤተ-ክርስትያን ያበረከተውን አስተዋፆ ከብዙ በጥቂቱ እንመለከታለን።

በምዕራፍ አንድ ላይ ቅዱስ አትናቴዎስ ከጫወታ የተጠራ በኋለም ከእለእስክንድሮስ እግር ስር ቁጭ ብሎ የተማረ በጉባዔ ኒቂያም ከመምህሩ ጋር መሳተፉም በአጠቃላይ ልደቱን እና እድገቱን ከተለያየ ማስረጃዎች ጋር ያቀረበ ሲሆን ለእኛም አርዓያ በሚሆን መልኩ ለበለጠ ጥናት እና ምርምርም በሚገፋፋ መልኩ ቀርቧል።

በምዕራፍ ሁለት ሰፊ ዳሰሳ የተደረገበት የኒቂያ ጉባዔ ሲሆን በዚህ ጉባዔ ላይ ቅዱስ አትናቴዎስ በዚህ ጉባዔ ላይ የአርዮስን ሀሳብ እንዴት ውድቅ እንዳደረገውና የሚጣፍጥ ኦርቶዶክሳዊ ትምህርቱን ካለው በትንሹ ቀርቦበታል። በዚህ ምዕራፍ ስለ ጉባዔ ቤቶችና ስለ እስክንድርያ ተካቶበታል።

በምዕራፍ ሦስት እና አራት የቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ፓትርያርክ መሆን ስለ ስደቱ እንዲሁም መዳሰስ ስላለባቸው አንዳንድ ታሪኮች ያካተተ ሲሆን ቅዳሴውንም በተወሰነ መልኩ የተመረጡ ጥቅሶችን አውጥቶ ያስቀምጣል። በመደምደሚያውም እንደዚህ ያለው ጥናት እንዴት ጠቃሚ እንደሆነና ሊበረታታ የሚገባው መሆኑን ይጠቅሳል። በመጨረሻም ያጋጠሙ ችግሮችን ጠቅሶ ያበቃል።

የጎደለውን እየሞላችሁ የተሳሳተውን እያረማችሁ በመንፈስ ሆናችሁ ታነቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ስም እንጠይቃለን።

አዘጋጆቹ


ምስጋና

የሁሉ ባለቤት ለሆነውና በኪሩቤል ጀርባ ላይ ነግሶ ለዘለዓለም ለሚኖረው መጀመሪያውና መጨረሻው ለማይታወቅ ጥበብን ለጠቢባን እውቀትን ለአስተዋዮች ለሚያድል አልፋ ኦሜጋ ተብሎ ለሚጠራው ለልዑል እግዚአብሔር ሁንልን።

ስንጠይቃቸው ሳይሰለቹን ላስተማሩን ለመጋቤ ምስጢር መሰረት ተሰማ እንዲሁም ይህንን ዳሰሳ እንድናዘጋጅ ላደረገን ለበረከት ጉዲሳ በተጨማሪም መጽሐፍ በመስጠት ሀሳብ በመለገስ የተሳሳትነውን በማረም ለተባበሩን ሁሉ በተለይ ለዲ/ን አቤል ሀይሉ እና ለከሳቴብርሃን ገብረኢየሱስ እግዚአብሔር እድሜ እና ጤና ሰጥቶ በቤቱ እንዲያገለግሉ ያድርግልን በጥበብ ይቃኝልን።

ምዕራፍ አንድ

የቅዱስ አትናቴዎስ ውልደት እና እድገቱ




ስዕል 1

ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ በ4ኛው ክፍለ ዘመን ከነበሩ የእስክንድርያ ቅዱሳን አባቶች መሀከል አንዱ ነው። አትናቴዎስ ማለት ሀያው ማለት ነው። ይህ ቅዱስ አባት 298ዓ.ም[1] በእስክንድርያ በግብጽ ተወለደ። ኤልሳዕ ከማሳው፣ አሞጽ ከበግ ጥበቃው፣ሐዋርያት ከአሳ አጥማጅነት ፣ ከቀራጭነት ከተለያዩ ግብር እንደ ተጠሩ ስለ አትናትዮስ ጥሪ በ4ተኛ መቶ ክ/ዘመን የነበረው የቤተ-ክርስቲያን ታሪክ ፀሐፊ ሩፊኖስ ሲናገር እንዲ ገልጾታል ‹‹ አትናትዮስ ሀጻን ሳለ ከሰፈሩ ሀጻናት ጋር ሆኖ ጓደኞቹ እንደ አዲስ አማኞች እየሆኑ ወደ እርሱ ይቀርባሉ። እርሱም ሥርዓት እያደረገ ያጠምቃቸዋል። ይህን ድርጊት በመፈጸም ላይ እንዳሉ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት እለእስክንድሮስ በሠገነቱ ላይ ሆኖ ተመልክቶ አንድም አልፎ ሲሄድ በመንገድ አጋጥሞት ነገሩ በጣም ስለደነቀው እና ጨዋታ ለበስ ምሥጢር ሆኖ ስላገኘው ሀጻናቱን አቅርቦ ምን ማድረጋቸው እንደሆነ ጠየቃቸው።እነርሱም በሥርዓተ ጥምቀት ተምሳሌት ይጫወቱ እንደነበር እና አጥማቂያቸው የነበረውን አትናቴዎስን ይህ ነው የሚያጠምቀን ብለው አሳዩት። ሊቀ ጳጳሱም ሀጻኑ አትናትዮስ ያጠመቀውን ጥምቀት በሜሮን አጽድቆ ተጠማቂዎቹን ሀጻናት ባርኮ አሰናበታቸው። አጥማቂውን ሀጻን አትናቴዎስን ግን ከእርሱ ጋር እንዲኖር ወደ መንበረ ፓትርያሪኩ ወሰደው። በመንበረ ፓትርያሪኩም ምሥጢረ ሀይማኖትን እየተማረ አድጎ ለማዕረገ ምንኩስና በቃ። በቅድስናው፣ በሙያው እና በግብረ-ገብነቱ እንከን የሌለው አትናትዮስ በተወለደ በ23 አመቱ በ318 ዓ.ም ሊቀ ዲያቆን ሆነ።[2]

[1] በዚህ በኩል እርግጥ ያለ ነገር ባይኖርም ነገር ግን 296-298 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ መወለዱን ብዙዎቹ ይስማማሉ።

[2] *የቤተ-ክርስቲያን ታሪክ በአለም መድረክ፣ የቅዱስ አትናትዮስ ሀዋርያዊ ሀይወቱ እና ትምህርቱ*

በሌላ የታሪክ ማህደር ቅዱስ አትናቴዎስ የትልቁ መሐመድ የልጅ ልጅ ልጅ ሲሆን አባቱ ሐነፊ ይባላል።



ሰንጠረዥ 1

ሐነፊ[3] አራት ልጆች የነበሩት ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ቅዱስ አትናቴዎስ ነው። የቅዱስ አትናቴዎስ ቤተሰቦች ከአረማዊ ነገድ የተገኙ ነበሩ። (በዚህ ላይ ሁለት አመለካከቶች አሉ አንዳንድ ምንጮች ከክርስቲያን ወገን ተወለደ [4] ሲሉ ቀደም ብለን እንደተመለከትነውም ከአረማዊ ወገን ነው እሚሉም አሉ እነዚን ሁለት ሀሳቦች አቡነ ጎርጎርዮስ እንዳሉት ‹‹ያም ሆነ ይህ ቅዱስ አትናቴዎስ ከጫወታ ሜዳ ተመርጦ የተጠራ የቤተ ክርስቲያን አባት ነው››[5] በሚል ወደ ፍሬ ሀሳቡ ብናዘነብል ይሻላል።)ብለን ቅዱስ አትናቴዎስ ልጅ እያለ የክርስትያን ልጆች ሥርዓተ-ቤተክርስትያን እየሰሩ ከእነርሱም ውስጥ ዲያቆናት፣ ኤጲስ ቆጶሳትን ሲያደርጉ የክርስቲያንን ልጆች ለመናቸው እነርሱም "አንተ አረማዊ ነህና ከእኛ ጋር አትደመርም" ብለው ከለከሉት እርሱም ክርስቲያን አሆናለው አጥምቁኝና አስገቡኝ ሲላቸው የጫወታ ጥምቀት አጠመቁት የጫወታ ሊቀ ጳጳስ አድርገው ሾሙትና ወንበር ላይ አስቀመጡት ሰገዱለት ፤ በዚያን ወራት የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ የነበረው እለእስክንድሮስ ነው ደቀመዛሙርቱን አስከትሎ መንገድ ሲሄድ የእነዚህ ህጻናትን ጫወታ በመገረም ቆሞ ተመለከተ፤አባታችን ከእነዚህ ህጻናት ምን ቁም ነገር ይገኛል ብለህ ትመለከታቸዋልህ አሉት፤እርሱም ይገኛል እንጂ ልጆቼ እነዚህ ህጻናት ያደረጉት በኃላኛው ዘመን እግዚአብሔር በእኔ ላይ አድሮ የሚሰራው ስርዓት ነው፤እነሆ በግብጽ ምድር ጽኑ ረሀብ ይከሰታል። የዚህ ህጻን አባቱ ይሞታል እናቱም እንዳሳድገው አምጥታ ለእኔ ትሰጠኛለች ከእኔ በኋላ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ የሚሆነው ይህ ህጻን ነው ብሎ ትንቢት ተናገረላት። በኋላም አባቱ ማለትም ሐነፊ በማረፋቸው ያለውን ሀብትና ንብረት ለድሆች መጽውቶ ወደ ሊቀ ጳጳሳት እለእስክንድሮስ ጋር ሄደ። የቤተ-ክርስቲያንን ትምህርት ህግና ሥርዓትንም ተማረ።(መፅሀፈ ስንክሳር)[6]

---

[3] ‹‹ አባቱ ሐኪም እናቱ ማርያም ትባላለች›› ስንክሳር ዘወርኃ ግንቦት 7

[4] ‹‹Athanasius was born to a christen family in the city of Alexandriya›› Wikipedia.org /wiki/Athanasius_of_Alexandriya

[5] የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአለም መድረክ ገፅ 91

[6] ስንክሳር ዘወርኃ ግንቦት 7

ስለ አትናትዮስ ብዙ መጽሐፍቶች ብዙ ጽፈዋል። ከእነርሱ ውስጥ ጥቂቱ ይህን ይመስላል። ቅዱስ አትናትዮስ ከፍ ተብሎ እንደተገለጸው በ23 አመቱ ሊቀ ዲያቆን ሆኖ ነበር። በዛን ዘመን ዲያቆን የሊቀ ጳጳሱ አፈ-ጉባኤ፣ ቀላጤ፣ እንደራሴ እንዲሁም ወኪል ሆኖ ያገለግል ነበረ። በዚህም ምክንያት አትናትዮስ ከሊቀ ጳጳሳት እለእስክንድሮስ ጋር ሆኖ ጉባኤ ኒቂያን ተካፈሏል።

ምዕራፍ ሁለት

ጉባኤ ኒቂያ

ሐዋርያት ሦስት አመት ከሦስት ወር ያጠኑትን ትምህርት ለአለም ለማስተላለፍ የረዳቸው ትምህርት ቤትን በማቋቋም ነበር። በቤተ-ክርስቲያን ታሪክ የሚታወቀው የመጀመሪያው ትምህርት ቤት ቅዱስ ኢያሮኒሙስ (ጀሮም) እንደዘገበው የእስክንድርያው ሲሆን በ60 ዓ.ም በቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ ተመሠረተ። ከሁሉም በፊት ስለ ታላቋ እስክንድርያ ትንሽ እንበል

2.1 እስክንድርያ

በግብፅ ሀገር ውስጥ ያለች የባህር ጠረፍ ከተማ ስትሆን በ 311 ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በፊት በታላቁ እስክንድር ለንግድ ማዕከልነት የተመሰረተች የጥንቱ ዘመን ታላቅ ከተማ ናት ። እስክንድር ከሞተም በኋላ የጦር መኪንኖቿ ግብጽን እየገዙ በነበረበት ጊዜ ሁሉ ዋና ከተማቸው እስክንድርያ ነበረች። በኋላም ከክርስትና መምጣት በኋላ ግብጽ በፋርሶች እና በአረቦች እስከ ወደቀችበት ጊዜ ድረስ እስከ 7ኛው መቶ ክፍለ-ዘመን የታላቁ የሮም ግዛት 2ኛ ዋና ከተማ ሆና ቆይታለች። ክርስትና ወደዚህ ከመግባቱ በፊት ከንግዱ በተጨማሪ የእውቀት መአከል ነበረች በውስጧም ሙዚየሞችና ታላላቅ መጽሐፍት ነበሩባት። አያሌ ፈላስፋዎችም ሆነ ሳይንቲስቶች የሚሰባሰቡባት ከተማ ነበረች።

በዚህም ከተማ የመጀመሪያው የእስክንድርያ ትምህርት ቤት የተመሰረተበት ነው። አላማውም አዲስ አማኞችን በቅዱሳት መጽሐፍት ትምህርት ለማሰልጠን እና ከዚያም ሲወጡ ወገኖቻቸውን ለማስተማር የሚያስችላቸውን መሠረታዊ እውቀት እንዲገበዩበት ነው። የንዑሰ ክርስቲያን ‹ የካታኪዝም› ትምህርት ቤት ነው። በ2ኛው እና በ3ኛው መቶ ክፍለ-ዘመን እየተስፋፋ ሄዶ መንፈሳዊ ብቻ ሳይሆን ፍልስፍናን ጨምሮ ማስተማር ጀመረ። እንዲሁም የትርጓሜ ትምህርትም ያስተምር ነበር።

የእስክንድርያው ትምህርት ቤት ከተነሳ አብሮ የሚነሳው በሶሪያ ዋና ከተማ በአንጾኪያ በሉቅያኖስ[7] በ3ኛው መቶ ክፍለ-ዘመን የተመሰረተው 2ኛው ትምህርት ቤት ነው።በዚህ ትምህርት ቤት

[7] ቁጥሩ ከመናፍቃን ወገን ነው ‹‹ Arius before Arius›› በመባል ይታወቃል።

ብዙ ፈላስፎች እየገቡ የክርስትናን ትምህርት ተምረዋል። በዚህ ጊዜ ደግሞ የፍልስፍናውን አስተሳሰብ የክርስትናውን ትምህርት በክሎታል። በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ ከተማሩት ውስጥ አንዱ አርዮስ ነው።

2.2 ቅድመ ኒቂያ

አርዮስ በ3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ በሊቢያ ተወለደ። ስለ ቤተሰቦቹ የተጻፈ ነገር ባይኖርም እርሱ ግን ክርስቲያን ነበር። አርዮስ ከቤተ-ክርስትያን ያጣላውን እና ለኒቂያ ጉባኤ መጠራት ዋነኛ ምክንያት የሆነው በአንጾኪያ በሉቅያኖስ ትምህርት ቤት ያገኘው ትምህርት ነበር[8]። በአንጾኪያ ትምህርቱን ከጨረሰ በኋላ ወደ እስክንድርያ በመምጣት ከተፍጻሜተ ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስ[9] የድቁና ማዕረግ ተቀበለ። ይህ አባት ድቁናውን ከሰጠው በኋላ በአርዮስ ልቡና የተደበቀው ተንኮልና የአርዮስ የወደፊት ሁኔታ በሱም ምክንያት ቤተ-ክረስትያን እንደምትቸገር ተገለጠለት።

ይህ ትልቅ አባት ከዕለታት በአንድ ቀን በራዕይ ቀሚሱ ለሁለት የተከፈለ ሀጻን መስሎ ጌታን ያየዋል ደንግጦም "አንተ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለህምን" ቢለው "አዎ ነኝ" አለው "ልብስህን ማን ቀደደብህ" ቢለው "አርዮስ ቀደደብኝ" ብሎታል ቅዱስ ጴጥሮስም አኪላስንና እለ እስክንድሮስን ጠረቶ ራዕዩን ነግሮ አርዮስን እንዳወገዘው ነገራቸው። ተፍጻሜተ ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስ በዲዮቅሊጥያኖስ ትዕዛዝ አንገቱ ተሰይፎ በሠማዕትነት ከአረፈ።[10] በኋላ አኪላስ መንበሩን ተረከበ። በዚህ ወቅት አርዮስን ተቀብሎ የተሰጠውን አደራ ትቶ የቅስና ማዕረግ ሰጠው። አኪላስም በዙም ሳይቆይ ለ አንድ አመት አስተዳድሮ ወድያው አረፈ። እሱን ተክቶ እለእስክንድሮስ ሊቀ ጳጳስ ሆነ እለእስክንድሮስም አርዮስን የክህደት ትምህርቱን ማስተማር እንዲያቆም ቢመክረውም ትምህርቱን ባለመተዉ ድርጊቱን ገፋበት።

ሊቀ ጳጳስ እለእስክንድሮስም አርዮስ ትምህርቱን የሚያሰራጨው ለህዝቡ በሚገቡት ቃላት ሃይማኖት አዘል የሆኑ ግጥም፣ጹሑፎች እያዘጋጀ ለእንጨት ሰባሪዎችና ለውሀ ቀጂዎች ለነጋዴው ላአራሹ ሁሉ በማደል ነበር። ሰዉም ከስድ ንባብ ይልቅ ግጥም ማንበብ ስለሚወድና ስለማይጠፋበት በዚህ እየተሳበ በአርዮስ ክህደት እየተሳሳተ ሄደ። ይህ ሁኔታ እየተባባሰ በመሄዱ ንጉስ ቆስጠንጢኖስ ወዳጁን ሊቀ ጳጳስ አርዮስን ወደ እስክንድርያ ላከው። እርሱም ጠቡ የግዝት እንጂ የአስተዳደር እንዳልሆነ አውቆ ወደ ንጉሱ በመመለስ ለንጉሥ አማከረው። ንጉሡም ቆስጠንጢኖስ ታላቅ ጉባኤ እንዲደረግ አወጀ። ጉባኤውም መጀመርያ ሊደረግ የታሰበው በዕንቁራ ነበር ነገር ግን ባልታወቀ ምክንያት በኒቂያ[11] እንዲደረግ ተወሰነ።[12]

2.3 በጉባዔ ኒቂያ ላይ....

[8] በዚህ ትምህረት ቤት ሳለ ‹‹ አርጌንስና ሉቅያኖስ መምህሩ ነበሩ›› የቤተ-ክርስቲን ታሪክ በአለም መድረክ ገፅ 75

[9] የዘመነ ሰማዕታት የመጨረሻው ሰማዕት በመሆኑ እና ሰማዕትነት በእኔ ይብቃ ብሎ በመጸለዩ ተፍፃሜተ-ሰማዕት ተሰኝቷል።

[10] 311 ዓ.ም

[11] የዛሬዋ ኢዝኒክ (ቱርክ ውስጥ የምትገኝ)

[12] የ ቤተክርስቲያን ታሪክ በአለም መድረክ

በጉባኤው 318 አባላቶች ከየ ሀገሩ በ325 ዓ.ም ተሰብስበዋል ። እነዚህም አባቶች በሕይወታቸው ንፅህና እና ቅድስና መሰል የሌላቸው ሃይማኖታቸውን በመመስከር እጅ እግራቸው የተቆረጠ አይናቸው የፈረጠ የቀና ሃይማኖት የነበራቸው ናቸው። ለምሳሌም ያክል ኤዎስጣጢዮስ ዘአንጾኪያ ፣ ያዕቆብ ዘነጽቢን መጥቀስ ይቻላል። እንደ ቶማስ ዘመርዓስ በዲዮቅልጥያኖስ ዘመን እግርና እጃቸው በተለያየ ጊዜ ተቆርጦ ወደጉባዔው የመጡት በቅርጫት ተደርገው በአህያ ተጭነው ነው። በጉባዔው እንዳይደርሱ የአህዮቻቸውን አንገቶች ቆርጠው ቢጥሉት ነጩን ለጥቁሩ ጥቁሩን ለነጩ ገጥሞ በጉባዔው ተገኝቷል።



ስዕል 2 (318ቱ ርቱዓን አባቶች)

ሀይማኖታቸው የቀና ምግባራቸው የፀና አባቶች በዚህ ጉባዔ እንደተሳተፉ ሁሉ የአርዮስ ደጋፊዎች ፈላስፋዎች ሳይንቲስቶች የአርጌንስ ትምህርት ተከታዮችም ጭምር ተገኝተው ነበር።

ጉባዔውን በሊቀመንበርነት እንዲመሩ የተመረጡት 3 ናቸው

1.የእስክንድርያው ሊቀ-ጳጳስ እለእስክንድሮስ
2.የአንጾኪያው ሊቀ-ጳጳስ ኤዎስጣቴዎስ እና
3.የእስፓኝ ኤጲስ ቆጶስ ኦስዮስ ናቸው።

ቅዱስ አትናቴዎስም ከእስክንድሮስ ጋር ተገኝቶ ነበር። በዚህ ጉባኤ ላይ ፀሀፊና አዘጋጅ ነበር። የአርዮስን ክህደት ውስጠ ምንነት ስለገባው የስህተቱን መሰረታዊ ፀረ-ክርስቲያናዊነት ለጉባኤው በማስረዳትና በማጋለጥ አርዮስንም ተከራክሮ በመርታት ከፍተኛ ድርሻ የነበረው በዚያን ግዜ የእስክንድርያው ፓትሪያሪክ ከነበረው ከቅዱስ እለእስክንድሮስ ጋር የሄደውና በወቅቱ ዲያቆን የነበረው ቅዱስ አትናቴዎስ ነበር።

2.4 አርዮስ ያነሳቸው ሀሳቦች በኒቂያ ጉባኤ

ወልድ ፍጡር ነው (እንደ ሌሎች ፍጡራን በገድልና በትሩፋት የአምላክነት ክብር አገኘ የሚል ነው**)** (ሎቱ ስብሐት)

አርዮስና ግብረ አበሮቹ የግሪኮችን ፍልስፍና ከመፅሀፍ ቅዱስ ጋር በማምታታት ለእነርሱ እንደሚመች አድርገው የተረጎሚቸው ጥቅሶች ማሰማት ጀመሩ ለምሳሌ፡- መፅሀፈ ምሳሌ ምዕራፍ 8፡25 ‹‹ተራሮች ገና ሳይመሰረቱ ከኮረብታዎች በፊት እኔ ተወለድኹ›› የሚለውን በማንሳት የወልድን ፍጡር መሆን (ሎቱ ስብሐት) ተከራክሯል።
ቅዱስ አትናቴዎስ ሀዋርያዊ አርዮስ ወልድ ፍጡር ነው(ሎቱ ስብሀት) ባለው ላይ መልስ ሲመልስ ሉቃ 15፡4-6 ላይ ያለው ‹‹የወልድ አምላክነት ከሰው ልጅ የመዳን ምስጢር ጋር የተያያዘ ነው። እርሱ አምላክ ካልሆነ ግን እኛም አልዳንም ማለት ነው። በእሱ መዳናችንን ካመንን ግን ያዳነን እሱ አምላክ መሆኑን ማመን እና ማወቅ አለብን ፍጡር ፍጡራንን ማዳን አይቻለውምና።..... የጠፋው በግ ለመላው የሰው ዘር የሚመለከት ነው ፈላጊው ቃል የ እግዚአብሄር ልጅ ነው። ቃል ፍጡር ነው (ሎቱ ስብሀት) ከተባለ የጠፋው ራሱ ራሱ ወልድ ነዋ!›› በማለት መልስ ሰጥቷል።

እንዲሁም አርዮስ በገድል በትሩፋት ስለከበረ የአምላክ ክብር አገኘ የሚለውን መልስ ሲሰጥ ክርስቶስ ከ ባሕርይ አባቱ ከአብ ጋር አንድ ነው ይህ ካልሆነ ደግሞ ፍጡር ነው (ሎቱ ስብሀት) ካልን ደግሞ ለሱ የ አምልኮ ስግደት አይገባውም የፀጋ እንጂ። ክርስቶስ በመዋእለ ሥጋዌው በሥጋ ርስት በሥጋዊ ሥርዓት ሐዋርያትን ደቂቀ አዳምን ወንድሞቼ ማለትን አያፍርም ወልደ እግዚአብሄር አዳም ሆኗልና። የአብ የባህርይ ልጅነቱን በተናገረበት አንቀፅ ግን ራሱን ከፃድቃንና ከሠማእታት ጋር ራሱን ቆጥሮ አባታችን አላለም፤ አባቴ አባታችሁ አለ እንጂ። አብ አባትነቱን በመሰከረበት ጊዜ ማለትም በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 3፡17 ‹‹ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው ›› አለ። በዮርዳኖስ ጌታችን ሲጠመቅ ብቻውን አልነበረም። ለምሳሌ ያህል መጥምቆ ዮሐንስ ነበር። ታዲያ አብ ሲናገር ዮሐንስንም ጨምሮ ልጆቼ አላለም?
እንዲሁም በማቴ17፡5 ላይ ‹‹ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ›› ይላል እዚህ ላይ ጌታችን ክብሩን በገለጠበት በደብረ ታቦር ከዮሐንስ፣ከያዕቆብ እና ከ ጴጥሮስ ጋር አዳብሎ ልጆቼ አላለም ለይቶ ልጄ አለው እንጂ በማለት ለአርዮስ የማያዳግም ምላሽ ሰጥቷል።

በመጨረሻም ጉባዔው ስለ ወልድ አምላክነት በባህርይ ከአብ ጋር አንድ ስለ መሆኑ አትናቴዎስ ያቀረበውን የመፅሀፍ ቅዱስ መረጃ አርዮስ ካሰባሰባቸው ጋር በማወዳደር ከተመለከቱና ካጤኑ በኋላ አርዮስ ወልድ ፍጡር በመለከቱ (ሎቱ ስብሀት) ለማለት ያበቃው ፍልስፍና፣ተራቀቅሁ፣አወቅሁ በማለት እንጂ ያቀረባቸው የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅስ ባለመኖሩ አርዮስ ሊወገዝ እና ወደ እስክንድርያም እንዳይሄድ ተወስኗል።
እሱን ካወገዙ በኋላ የቢተክርስቲያንን እምነት ከፍልስፍና ለይተው እና በመፅሀፍ ቅዱስ ቃል የሚለውና ወልድ የሚለው አንድ መሆን አብራርተው የወልድንም መገናኘት አትናቴዎስ እንዳቀረበው አካል ዘእምአካል ባህርይ ዘእምባህርይ አብን አህሎ አብን መስሎ ከአብ ተገኘ ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ አያሳንሰውም በማለት የመለኮት አንድነት፣የአካላትን ሦስትነት የወልድንም አምላክነት በመፅሀፍ ቅዱሳዊ አንቀፀ ሀይማኖት አፅድቀዋል። ይህም ጸሎተ ሐይማኖት 7 አንቀጾችን ያጠቃለለ ነው። እነሱም፡-

1. ሁሉን በያዘ ሰማይና ምድርን በፈጠረ የሚታየውንና የማይተየውን በፈጠረ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን።

2. ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ ጋር በነበረ በአብ አንድ ልጁ በሚሆን በአንድ ጌታ በ ኢየሱስ ክርስቶስም እናምናለን።
3. ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ የተፈጠረ አይደል የተወለደ በመለኮቱ ከአብ ጋር የሚተካከል።
4. ሁሉ በእርሱ የሆነ ያለ እርሱ ምንም ምን የሆነ የለም በሰማይም በምድርም ያለ።
5. ስለኛ ስለ ሰዎች ስለመዳናችን ከሰማይ ወረደ። በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከቅድስት ድንግል ማርያም ፈፅሞ ሰው ሆነ።
6. ሰው ሆኖ በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን ስለእኛ ተሰቀለ ታመመ ሞተ ተቀበረም። በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሳ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈ።
7. በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ። ዳግመኛም ሕያዋንን እና ሙታንን ይገዛ ዘንድ በጌትነት ይመጣል። ለመንግስቱም ፍጻሜ የለውም።
   እስከሚለው ነው ቀሪው የጸሎተ ሐይማኖት ክፍል በቁስጥንንያ ጉባዔ የተወሰነ ነው።[13] [14]

[13] 8. ጌታ ማኅየዊ በሚሆን ከአብ በሠረፀ በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን እንሰግድለት እናመሰግነውም
9. ዘንድ ከአብና ከወልድ ጋር በነብያት የተናገረ።
10. ከሁሉ በላይ በምትሆን ሐዋርያት በሠሯት በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም እናምናለን።
11. ኃጢያት በሚሠረይባት በአንዲት ጥምቀት እናምናለን።
12. የሙታንን መነሳት ተስፋ እናደርጋለን። የሚመጣውንም ሕይወት ለዘላለሙ አሜን።

[14] **<u>ጉባዔ ቁስጥንጥንያ (381 ዓ.ም)</u>**

በዚህ ጉባዔ በዋናነት የተከሰቱት ክስተቶች የመቅዶኔዎስ፣የአቡሊናርዮስ እና የጸሎተ-ሃይማኖት አሁን ያለውን መሉ ነገር እንዲይዝ መደረጉ ነው። መቅዶኔዎስ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ምንፍቅናን የተናገረ መናፍቅ ነው እሱም ‹‹መንፈስ ቅዱስ ሕጹጽ ነው›› (ሎቱ-ስብሐት) ብሎ በድፍረት ያስተማረ ሲሆን በ 381 በቁስጥንጥንያው ንጉስ ቴዎዶስዮስ ይህን የሐይማኖት ችግር የሚፈታ ጉባዔ በቁስጥንጥንያ እንዲደረግ ታወጀ። በዚህም ምክንያት 150 ሊቃውንት ኤጲስ ቆጶሳት በቁስጥንጥንያ ተሰባሰቡ በሊቀመንበርበትም ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ፣ ኔክታሪዮስ እና ጢሞትዮስ (ዘአልቦ ጥሪት) በተለያዩ ጊዜያት አገልግለዋል። የመቅዶንዮስ ትመህርትም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ የሌለው በመሆኑ ኢሳ 6 በመመልከት በባህሪ በመለኮት እኩል መሆናቸውን ወስነው መቅዶኔዎስን አውግዘዋል። የ አቡሊናርዮስ ምንፍቅና ደግሞ ‹‹ ወልድ ስጋን እንጂ ነፍስን አልነሳም›› የሚል ነበር ነገር ግን ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ሲመልስለት


‹‹ ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ያልተዋሃደውን አላዳነውም ስጋን ብቻ ተዋሃደ ካልን ንፈስን አላዳናትም ማለታችን ይሆናል›› ብሎ መልሶለታል በዚህም እሱንም እንደ መቅዶኔዎስ አውግዘው ለይተውታል።

በመጨረሻም በዚህ ጉባዔ የተሰራው የሰለስቱ ምዕት ፀሎተ ሃይማኖትን አፅድቆ ምስጥሩን ሳይሆን ንባቡን አስተካክሎ ከዛም አዲስ ባለ አምስት አንቀፅ ማለትም ‹‹ከጌታ ማኅየዊ በሚሆን ከአብ በሠረፀ በመንፈስ

በመጨረሻም የኒቂያ ጉባኤ አርዮስን በማውገዝና የ ቤተክርስቲያንን ቀኖናን ሰርተው ጉባኤው ተጠናቋል።

ምዕራፍ ሦስት

<u>የቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ፓትርያርክ መሆን</u>



ስዕል 3

ከኒቂያ ጉባኤ በኋላ በ328 ዓም ሊቀ ጳጳስ እለእስክንድሮስ በማረፉ ምክንያት ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ሊቀ ጳጳሳት ሆኖ ተሾመ። እርሱ ግን ሹመትን ሽሽት ተሸሽጎ ነበር የህዝቡ ጥያቄ ስላየለ በማርቆስ ወንበር 20ኛ ፓትሪያሪክ ሆኖ ተሾመ። ገና በወጣትነት ዘመኑ ቤተ ክርስቲያን ከአርዮሳውያን ጋር በከባድ ተጋድሎ ላይ ስለነበረች ወሳኝ ጊዜ ላይ ከባዱን ሃላፊነት ተሸከመ። ቆንጠንጢኖስ አርዮስን ከስደቱ ከመለሰው በኋላ የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን እንድትቀበለው ወደ እስክንድርያ ላከው። ቅዱስ አትናቴዎስም ንጉሡ በአርዮስ ጉዳይ ላይ ጣልቃ መግባቱን በመቃወም ውግዘቱም ሆነ መፈታቱ በቤተክርስቲያን እንጂ ቤተ-መንግስትን እንደማይመለከት ለንጉሱ አለመቀበሉን ተናገረ። የአርዮስ ወዳጅ የነበረው ኒቆሞዲያ ሊቀ ጳጳስ አውሳብዮስ ከንጉሡ ከ ቆስጠንጢዮስ ጋር ወዳጅ የነበሩ በመሆኑ ታላላቅ አባቶችን ከንጉሡ ጋር በማጣላት ከጵጵስናቸው እንዲወርዱ ተደረገ።

ቅዱስ አትናቴዎስ ከእነዚህ አባቶች መሀከል አንዱ ነበር። የአርዮስ ተከታዮች በኒቂያ ጉባዔ በደረሰባቸው ውርደት ቅዱስ አትናቴዎስን ሊበቀሉ ይፈልጉ ነበር ። አርዮስን ባለመቀበሉ ምክንያት አርዮሶች (የአርዮስ

ቅዱስም...›› እስከ ‹‹....የሚመጣውንም ሕይወት ለዘላለሙ አሜን።›› (8-12) እሰከሚለው ድረስ አርቅቆ ጉባዔው ተጠናቀቀ።

እንግዲህ ከላይ እንደተመለከትነው በ12ቱ የጸሎተ ሃይማኖት አንቀፆች ውስጥ የሚስጥረ ስላሴ፣ የሚስጥረ ስጋዌ፣ ሚስጥረ ጥምቀት ትንሰዔ ሙታን ባጠቃለይ ብዙ ሚስጥራትን እና ሰፊ ትምህረትን የያዘ በመሆኑ ሁላችንም በፀሎት ሰዓት በቅዳሴ በጥምቀት ጊዜ(ክርስትና አባት ወይም እናት በክርስትና ጊዜ በህፃኑ ፋንታ እንዲሉ) ልንለው (ልንደግመው) ይገባል።

ተከታዮች) አትናቲዮስን ከንጉሱ ጋር ለማጣላት ዘዴ አገኙ። አውሳቢዮስ ለንጉሱ አትናቴዎስ አርዮስን አልቀበልም እንዳለ ነገሩት ንጉሱም ለአትናቴዮስ ወደ ቤተክረስቲያን ሊመለሱ የሚፈልጉትን ሁሉ ካልተቀበልክ እኔ ራሴ ሰው ልኬ ከመንበርህ አወርድሃለው የሚል ማስጠንቀቂያ እንዲላክበት አደረገ። አትናትዮስ ግን ‹‹ የክርሰቶሰ ጠላት የሆነው አርዮስ እና ኑፋቄው ከኦርቶዶክሳዊት ቤተ-ክርስቲያን ጋር ምንም ህብረት የላቸውም ›› በማለት በድጋሜ የንጉሱን ትዕዛዝ አልቀበልም አለ።

ይህ ሁኔታ ለአርዮስ ደጋፊዎች በተለይ ለአውሳቢዮስ ሁለቱን ለማጣላት ቀላል ሆነለት በኋላም ታግሶ ሊያልፋቸው ቀርቶ ሊሰማቸው እንኳን በሚዘገንኑ የፈጠራ ክሶች ከወነጀሉት በኋላ የቂሳርያ ጳጳስ ከነበረው አውሳቢዮስ ዘቂሳርያ ጀምሮ ግልጥ አርዮሳዊያን የሆኑ ብዙ የቅዱስ አትናቴዎስ ጠላቶች ባሉበት በፍልስጤም ቂሳርያ ጉባዔ እንዲጠራ ለመኑት ንጉሱ የአርዮሳዊያንን ተንኮል ስላላወቀና ነገሩ እውነት ስለመሰለው በነገሩት መሰረት የፈለጉት ጉባዔ እንዲጠራ ትዕዛዝ ሰጠ ። ቅዱስ አትናትዮስ ግን ፈራጆች ሆነው በጉባዔ ሊቀመጡ ያሰፈሰፉት ጠላቶቹ እንደሆኑ ጠንቅቆ ስላወቀ ‹‹ ከሳሾቼ ዳኞች በሆኑበት ጉባዔ አልገኝም ›› አለ እነሱም የአትናቴዎስን አለመገኘት አጋነው ለንጉሱ በመንገር ንጉሱም የጉባዔው ቦታ በቂሳርያ መሆኑ ቀርቶ በጢሮስ እንዲሆን እና በዚህ ጉባዔ ባይገኝ ግን በግድ እንዲገኝ የሚያደርገው መሆኑን በቁጣ መልዕክት ላከበት

የጢሮስ ጉባዔ እና ክሶቹ

የአርዮስ ደጋፊዎች በዚህ ጉባዔ ላይ አትናትዮስን በ4 ክሶች ወንጅለውታል።

1. በነፍሰ ገዳይነት፡- ሊቀ ጳጳስ አርሳንዮስን ገድሎታል እጁን ለመተት ይጠቀምበታል በማለት ከሰውታል
2. በድብደባ ወንጀል
3. በዝሙት አግኝተነዋል በማለት
4. ፖለቲካን በሚመለከት ከሰሱት

በዚህ ጉባዔ ላይ ከሳሾቹ እና ዳኞቹ እራሳቸው አርዮሳዊያን ነበሩና በጢሮስ መቆየት ለህይወቱ በጣም አስጊ መሆኑን ስለተገነዘበ ጠላቶቹ የሆኑት ዳኞች ፍትሀዊ ዳኝነት እንደማይሰጡት ስላወቀ ወደ ቁስጥንጥንያ ሄደ። ቅዱስ አትናትዮስም ቁስጥንጥንያ ከንጉስ ቆስጠንጢኖስ ዘንድ በመሄድ በጢሮስ ተደረገውን በመንገር እርሱ ባለበት እንዲታየለት ተማፀነ።

ንጉሱም እንደገና እርሱ በሚገኝበት ጉባዔ እንዲገኙ መልዕክት ለሁሉም ላከ። የአርዮስ ደጋፊዎች በሁኔታው ቢደናግጡም አዳዲስ ክስና ውንጀላ አዘጋጅተው በጉባዔው ተገኙ። በዚህኛው ጉባዔ ዋነኛ ክሳቸው የነበረውን እንዲህ በማለት አሠምተዋል ‹‹ በየአመቱ ከእስክንድርያ ወደ ቁስጥንጥንያ እህል ጭነው የሚሄዱትን መርከቦች እንዳይጓዙ በመከልከል የንጉሱን ከተማና ህዝብ የረሀብ አደጋ እንዲጋረጥበት አደርጋለው እያለ ሲዝት ነበር አሉ።›› ቅዱስ አትናትዮስ ይህን ለማድረግ ፍላጎቱም ሆነ አቅሙም እና ስልጣኑም የለኝም በማለት ሲያስረዳ አውሳቢዮስ ዘኒቆሞዲያ ‹‹ አንተ ባለፀጋ ሰው ነህ

እናም የፈለከውን ማንኛውንም ነገር ማድረግ ትችላለህ›› በማለት መለሠ ንጉሱ ቆስጠንጢኖስ በስስ ቆዳው እንደተወጋ ሰለተሰማው ፍትሀዊ ችሎት ማስኬዱ ቀርቶ ትሬቭስ ወደ ሚባል ቦታ እንዲሰደድ ወሰነበት።

3.1 ስደቱ

ቅዱስ አትናቴዎስ ፓትሪያሪክ ኮሆነ ጊዜ አንስቶ አምስት ጊዜ በስደት ተቀምጧል ። ከዚያም በረሃ ለ2 ዓመት ከ4ወር በሰደት ከቆየ በኋላ ቆስጠንጢኖስ ሲሞት ለዳግማዊ ቆስጠንጢኖስ ማለትም በቆስጠንጢኖስ ልጅ ተመለሰ። ቅዱስ አትናትዮስ ከስደቱ ከተመለሰ በኃላ የቆየባቸው ጊዜያት አጭርና በችግር የተሞሉ ነበሩ። ከዚህ በኋላ አርዮሳዊያን በአውሰቢስ ዘኒቆሞዲያ እቅድ በኦርቶዶክሳዊያን ላይ በመሪነት የሚያደርጉትን ዘመቻ አጠናክረው ቀጠሉ በተለይም ንጉስ ቆስጠንጢኖስ ቀዳማዊ መሞት ፣ የሮም ግዛት ከሦስት መከፈል የበለጠ ምቹ ሀኔታን ፈጠረላቸው። ቆስጠንጢኖሰ ዳግማዊ እና ቁንስጣ ኦርቶዶክሳዊያን ሲሆኑ ቁንስጣንዲዩስ ግን ወላዋይ ነበር። በመሆኑም እርሱ በሚያስተዳድርበት ቦታ እንቅስቃሴ ጀመሩ ።

ስራቸው ፈር ይዞላቸው ቅዱስ አትናቴዎስን ከድጅስናው አውርደው እነዲያባርረው መንገድ ከፈቱለት እርሱም በነገራቸው ተስማምቶ አትናቴዮስን አውርዶ በምትኩ ጎርጎርዮስ የተባለ የአርዮስ ተከታይ ሾመ። ቅዱስ አትናቴዎስ በሁለተኛው ስደቱ 7 ዓመት ከ 6ወር ከቆየ በኃላ ቆንስጣ በቅዱስ አትናቴዎስ ላይ የደረሰበትን ተመልክቶ ለወነድሙ ወደመንበሩ ይመልሰው ዘንድ እንዲሁም እንደፈለጉ የሚፈነጩትን አርዮሳዊያንን ስርዓት እንዲያሲዛቸው ጠንካራ መልዕክት ላከበት ቆስጣንዲንዮስም የወንድሙን መልዕክት ተቀብሎ አትናቴዎስን መለሰው።

ከዚህም በኋላ ቅዱስ አትናቴዎስ ለ አስር ዓመታት ያክል በሰላም ያስተዳድር ጀመር። ይህም ጊዜ ‹‹ ወርቃማው ጊዜ ይባላል›› ነገር ግን ንጉስ ቆንስጣንድንዮስ ኃይሉን አጠናክሮ ሁሉንም ግዛት ጠቅልሎ መግዛትና ብቸኛ ንጉስ መሆን ጀመረ በዚህ ጊዜ እንደገና አትናቴዎስን ማሳደድ ጀመረ በዚህ ጊዜ እንደገና አትናቴዎስን ማሳደድ ጀመረ። በዚህም ምክንያት አትናትዮስ ለሦስተኛ ጊዜ ተሰደደ በዚህም ስደቱ ስድስት አመት ቆየ በዚህም ጊዜ ታላላቅ የጽሑፍ ስራዎችን የጻፈው በዚህ ወቅት ነበር። ከነዚህም መካከል

1. በአርዮሳዊን ላይ የጻፈው አራት ጥልቅና መሰረታዊ የሆኑ ዶግማዊ ጹሑፎች
2. ዶግማዊ ደብዳቤዎች
3. በእንተ ሲኖዶሳት የሚሉትነ ይጠቀሳሉ።

ከዚህ በኋላ ንጉሱ በንዳድ ምክንያት ታሞ ሞተ በምትኩመ ጁሊያን ነገሠ። ጁሊያን በጊዜው ደግ ሰው ለመምሰል ጥረት አደረገ በዚህም ተሰደው የነበሩተን አባቶች ወደ መንበራቸው መመለስ ጀመረ። ቅዱስ

አትናቴዎስም በዚህ ጊዜ ከስደት ተመለሰ ብዙም ሳይቆይ ግን ቅዱስ አትናቴዎስ በዚሁ ንጉስ 4ተኛ ስደቱን ተቀበለ ከዚያም በግብፅ ገዳማት ካሉ መነኮሳት ጋር ቆይቷል። ከዚያም ንጉሱ ጁሊያን ሞቶ ክርስቲያን የሆነው ንጉስ ጆቪያን ነገሰ ነገር ግን ‹‹ ደና ሰው አይበረክትም እንደሚባለው ›› ምንም አትናቴዎስን ከግዞት ቢያስፈታውም ጆቪያን በድንገት በነገሰ በ 8ወር ሞተ ። በዚህም ምትክ ቫሌንቲያን ነገሰ እርሱም ወንድሙን ቫሌንስን እንዲረዳው አነገሰው። ቫላንቲያን ፀረ-ኦርቶዶክሳዊ ሲሆን ቫሌንስ ደግሞ የፀና ሐይማኖት አልነበረውም በዚህም ምክንያት ለ5ተኛ ጊዜ ተሰደደ። ነገር ግን ይሔኛው ስደቱ አጭር ነበር ወዲያው በወንድሙ ቫሌንስ አማካኝነት ተጠርቷል።

ቅዱስ አትናትዮስ ጳጳስ ሆኖ ከተሾመ በኋላ ለ47 ዓመታት ቤ/ክ አገልግሏል። ከዚህ ውስጥ 16 ዓመት የሚሆነውን በስደት አሳልፏል። ይህ የእምነት አርበኛ የቤተ-ክርስቲያን ጠበቃ በ75 ዓመቱ ግንቦት 7 ቀን 373 ዓ.ም ድካምና ውጣውረድ የተሞላውን የአለም ህይወት ፈጸመ።

ምዕራፍ አራት

ስለ አትናቴዎስ

- ቅዱስ አትናቴዎስ ለምን ሐዋርያዊ[15] ተባለ?
  ሐዋርያ የተባለበት መክንያት ህይወቱ እንደ ሐዋርያት ስለነበር ከመናፍቃን ጋር ተጋድሎ የፈፀመ ሲሆን ለሐዋርያት ባሰራው ቦታ እየጸለየ ሳለ ሐዋርያት ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልከው አንተ የተመሰገንክ ነህ ሐዋርያዊ ትባለላህ ብለውታል ።
- ጸሎተ ሐይማኖተን ከሠለስቱ ምዕት ጋር ጽፏል።
- ብዙ መልዕክቶችን ጽፏል በብዛት የሚታወቁት የፋሲካ መልዕክቶቹ ናቸው። እነዚህ መልዕክቶች በፋሲካ ሰሞን ስለ ጾሙ እና በተለያዩ አርዕስቶች ዙርያ የያዙ ናቸው። በነዚህም በግብጽ የሚገኙትን የግሪክ ቤተ-ክርስቲያኖች የፋሲካን ጾም 40 ቀን እንዲጾሙ አድርጓቸዋል።
- የአባ አንጦንዮስን ገድል የጻፈ እርሱ ነው። አባ እንጦንዮስ የመጀመሪው መነኩሴ ነበር ምንኩስናን ልብስ መልአኩ ሚካኤል አልብሷቸዋል። ቅዱስ አትናቴዎስም በስደቱ ጊዜ በእርሳቸው ጋር እንዳረፈ ይነገራል
- የመጀመሪያውን የኢትዮጲያ ጳጳስ አቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃንን ሾሞ የላከልን ቅዱስ አትናቴዎስ ነው።

15



ስዕል 4 (አቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን)

- የመጽሐፍትን ቀኖናም የሀዲስ ኪዳንን በ27 መጽሐፍት ብሉይ ኪዳንንም በ22 መጽሕት ቀኖና ሰርቷል።
- በተለያዩ እምነቶች የሚቀበሉት አባት ነው። የራሳቸውንም ስም ይሰጡታል
  - ✓ <<Doctor of the church>>……roman chatholic church
  - ✓ <<Father of orthodoxy>>…….estern orthodox church
  - ✓ << father of canon >>…… protestants
  - ✓ << pillar of the church >> ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ
- አትናትዮስ ለፍልስፍናው ቅርብ ነበር ይህም በተለየ በጻሐፋቸው መጽሐፎቸሁ የሆሜር አባባሎችን ይጠቀም ነበር።
- በእስክንድርያ ትምህርት ቤት የቃል ሽምደዳ በቃል የማጥናቱ ነገር ያመዝናል በዚህም አርዮስ በስደት በነበረበት ጊዜ መልዕክታትን ለመጻፍ ምንም አልተቸገረም ሁሉንም በቃሉ ያውቅ ነበር።

❖ ቅዳሴ አትናቴዎስ

ከ14ቱ ቅዳሴያት አንዱ ሲሆን በእለተ ቀኑ ማለትም ግንቦት 7 ይቀደሳል። በእለተ ሰንበት ይቀደሳል።[16] የጌታችን ምጽአት (ደብረ-ዘይት) ፣ጳጉሜ እሁድ ከዋለች ሰንበት ይቀደሳል። ባገኘነው መረጃ መሰረት ሰንበተ ሰንበታት[17] በተባሉ ሰንበታት ይቀደሳል።

- ‹‹ ሙሴን ከተጠሉት እንደ ዳታን እና እንደ አቤሮን ከባለንጀራው ጋር ማንም በመጣላት ከዚህ አይኑር›› ቅ.አት ምዕ. 6
- ‹‹ ወዮ ይህች ዕለት አብ የቀደሳት ወልድ የባረካት መንፈስ ቅዱስ ከፍ ከፍ ያደረጋት ናት በእርሷ ደስ ይበለን በእርሷም ሃሴት እናድርግ ትከብሩባት ዘንድ አክብሯት›› ምዕ 75
- ‹‹ ወዮ ይህች ዕለት ያረጀችዋ ያለፈችባት አዲሲቱ የጸናችባት ናት ወዮ ይህች ዕለት እስረኞች (ነፍሳት) የተፈቱባት ባሮች ነፃ የወጡባት ናት።›› ምዕ 76
- ‹‹ ሰውስ የብርሃን ልብስ የለበሰ ሲሆን ሰውነቱን አራቁቶ የዳባ ልብስን ለበሰ››
- ‹‹ የበዓላትን በኩር ኑ ከፍ ከፍ እናርጋት ኑ እናመስግናት ይህችውም ሰንበት ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን ናት››
- ‹‹ ያን ጊዜ ጻድቃን ደስ ይላቸዋል በህይወታቸው አልቅሰዋልና ታጥአን ያለቅሳሉ ሳቅና ሥላቅን ስለወደዱ የፍርድና የፍዳ ቀን ደርሳባቸዋለችና.....ያን ጊዜ ታያልን ለምሾ ይሆናሉ እጃቸውን ለመቀማት ዘርግተዋልና ባልቴትና አባት እናት የሞቱበትን አስለቅሰዋልና››

[16] ይህ የሚሆነው በጾም ወቅት ካልሆነ እነዲሁም በዓል ካልሆነ ነው።

[17] ሰንበተ ሰንበታት የራሳቸው አቆጣጠር አላቸው። ከሌሎቹ ሰንበታት የሚለየው በዓላት ስለሚውሉበት ነው። ለምሳሌ የእመቤታችን መታሰቢያ 21 ሰንበት ላይ ከዋለ ሰንበተ ሰንበታት ይባለል። በዚህ አቆጣጠር መሰረት ሊቃውንቱ ከግፃዌ ፣ ከድጓ ፣ ከመዝሙረ ዳዊት ንባባት ጋር በማስተያየት ቅዳሴውን ያስቀምጣሉ። በ 7 ዓመት አንድ ጊዜ የሚደርሰው የመዝሙረ ዳዊት ክፍል አለ። (ቆሞስ አባ ወልደ ትንሳኤ)

መደምደሚያ

ይህንን ዳሰሳ ስናጠቃልል ቅዱሰ ሐዋርያዊ አትናቴዎስ የእስክንድርያ ቤተ-ክርስቲያን 20ኛው ፓትርያሪክ ይሔንን ዳሰሳ ለሰራን ትልቅ ትምህርት እና የህይወት ስንቅ ሆኖናል። ቅድስናው ህይወቱ አስተምህሮው ትልቅ ትምህርት የሆነ ታላቅ አባት ነው። ይሔንን ዳሰሳ ለእናንተ ስናቀርብ እኛ የቀሰምነውን እውቀት እናንተም እንደምትማሩበት ተስፋ በማድረግ ነው።

ይህ ዳሰሳ እጅግ ጠቃሚ እና ይበል እሚያስበል ነው። እናም እነደዚህ አይነት ዳሰሳውችን በተጠና መልኩ ቢቀጥሉ እና ቢስፋፉ በተለይ ለወጣቱ እጅግ በጣም ጠቃሚ ነው። በዚህ ጥናት ውስጥ እኛ ብዙ ነገሮችን ተጠቅመናል አባቶችንም ጠይቀናል ወንድሞችን አማክረናል እውቀትን ፍለጋ ጥረናል። በዚህ ሁሉ መካከል እንዴት መጠየቅ እንዳለብን እንዴት ቅዱሳን መጽሐፍትን መመርመር እንዳለብን ጭምር በሚገባ ተምረናል።

ይህን የመሰለ ጥቅም የሚሰጥ ስራ በተደራጀ መልኩ በሰንበት ትምህረት ቤቶች ፣ በማህበራት ፣ በጉባዔዎች ቢቀጥል እንላለን።

የግጠሙን ችግሮች

- እንዲህ ዓይነት ጥናታዊ ጽሑፎች ሥራ ለእኛ የመጀመሪያ እንደመሆናቸዉ እንዲሁም እንዲህ ዓይነት ጥያታዊ ጽሑፎችን ለማስተያያነት አለማግኘታችን
- የመጽሐፍ እጦት ትልቁ ፈተናችን ነበር።
- ቅዱስ አትናቴዎስ የጻፋቸዉ ከግእዙም ይሁን ከኢንግሊዘኛ ቋንቋ አለመተርጎማቸዉ እንዲሁም እንደልብ አለማግኘታችን
- በታሪክ ጉዳይ ላይ ተራኪዎቹ ያቀረቧቸዉ ሃሳቦች መጣረስ

ዋቢ መጻሕፍት

1. መጽሐፍ ቅዱስ 81
2. ስንክሳር
3. የቤተክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ (አባ ጎርጎርዮስ)
4. የቤተክርስቲያን ታሪክ በኢትዮጵያ(አባ ጎርጎርዮስ)
5. የቤተክርስቲያን ታሪክ (ሉሌ መላኩ)
6. የቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያ መልእክታት(
7. የቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያ ሕይወቱና አስትህሮቱ(ዲ/ን ያረጋል አበጋዝ)
8. Wikipedia.org /wiki/Athanasius_of_Alexandriya